# በትራንስፖርት ባለሥልጣን

## በብቸኝነት የሚሰጡ መስመሮችን በተመለከተ የተዘጋጀ የአሰራር ስርዓት

## የተሻሻለ

672/2013

ሚያዝያ 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


1. የሰነዱ መነሻ ሁኔታ ..... 2
2. የሰነዱ ዓላማ ..... 2
3. በሁሉም ማህበራት ፕሮግራም ወጥቶላቸው የማይሸፈኑ መስመሮችን በብቸኝነት ለመስጠት፣ ..... 3
4. በትራንስፖርት ባለሥልጣንና በክልሎች እንዲሁም በማህበራት በጋራ ተጠንተው የሚከፈቱ መስመሮችን በተመለከተ፡- ..... 5
5. በማህበር በግል ተጥንተው ስለሚከፈቱ የብቸኝነት መስመሮች ..... 6
6. የብቸኝነት መስመሮችን በጋራ ስለመስራት ..... 8
7. የብቸኝነት መስመር የቆይታ ጊዜ ..... 9
8. የብቸኝነት መስመር በጨረታ/ውድድር ለመስጠት፣ ለማጥናት እና ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የማስተናገጃ ጊዜ ..... 10
9. የአሰራር ስርዓቱ ተግባራዊነት ..... 10
10. የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን ..... 10
11. ይህ የአሰራር ስርዓት የሚፀናበት ጊዜ ..... 10

# I. መግቢያ

የአገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ማህበራት በጋራ በሚያወጡት የመደበኛ ፕሮግራም መሠረት ስምሪቱ እየተሰጠ የሚገኝ ቢሆንም በጋራ በወጣው ፕሮግራም መሠረት በሁሉም መስመሮች አገልግሎት የማይሠጥባቸው ሆኖ በመገኘቱ በእነዚህ የማይሸፈኑ መስመሮች ላይ እንዲሸፈኑ ለማድረግ ወጥ አሰራርን ዘርግቶ ተደራሽነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ ፕሮግራም ወጥቶላቸው በተፈለገው ጊዜና ወቅት ሲሸፈኑ የማይችሉትን መስመሮች በመለየት እያንዳንዱ ማህበር በተናጠል /በብቸኝነት/ በውል አግባብ እንዲወስዳቸው በማድረግ በመስመሮቹ ላይ ተጨማሪ የማነቃቂያ ስርዓት በመፍጠር መስመሮቹ እንዲለሙና ዘለቀታዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ማህበር በራሱ ተነሳሽነት ጥናት በማካሄድ ሌሎች ተጨማሪ መስመሮች በብቸኝነት የሚይዝበት ሁኔታ የሚያመቻች ሲሆን በዚህ ረገድ የባለሥልጣን መ/ቤቱም በስታራቴጂ ዘመኑ የያዘውን ዕቅድ ለማሳካት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና ተደራሽነትን የሚያረጋግጥ ሲሆን ትራንስፖርት ፈላጊውን ሕብረተሰብ ደግሞ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያግዝ መሆኑ ታምኖበት ይህ የአሰራር ስርዓት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

672/2013

# 1. የሰነዱ መነሻ ሁኔታ

1.1. በመደበኛው የፕሮግራም ስምሪት የተወሰኑ መስመሮች በፕሮግራም ሳይ ከመካተታቸው ውጭ አገልግሎት መስጠት ያስመቻላቸው፣

1.2. በየጊዜው ተጨማሪ መስመሮች መክፈት አስመቻል፣

1.3. አገልግሎት የሚሰጡ አገር አቋራጭ ተሽከርካሪዎች ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም ተጨማሪ የጉዞ መስመሮች የመክፈት ሂደት አዝጋሚ በመሆኑ ከተደራሽነት አንፃር ውስንነቶች መታየታቸው፣

1.4. እስከ አሁን ባለው ሂደት በብቸኝነት የተሰጡና የተከፈቱ መስመሮች ውጤታማ በመሆናቸውና ይህንን በህግ የአሰራር ስርዓት አስፈላጊ በመሆኑ ስመደገፍ፣

# 2. የሰነዱ ዓላማ

መስመሮችን በብቸኝነት መስጠት ያስፈስገበት ምክንያት የተወሰኑ መስመሮች በፕሮግራም ተካተው በትራ/ማህበራት/ድርጅቶች ባስመሸፈናቸውና ተደራሽነትን ማረጋገጥ ባስመቻላቸው የዚህ ሰነድ አላማ ከዚህ በታች ባሉት መሰረተ ሀሳቦች ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል::

2.1 በህዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ ከተቀመጠው የGTP ዕቅድ የመስመርና፣ የኪሎ ሜትር ሽፋንን ስማሳካት እና ተደራሽነትን ስማረጋገጥ፣

2.2 በአገሪቱ ውስጥ በመደበኛ ስምሪት ሽፋን ያላገኙ አካባቢዎችን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት በመዘርጋት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ስማድረግ፣

2.3 በአሠራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት ያለው የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር ስማድረግ፣

2.4 አሳታፊና ተጨማሪ መስመሮች እንዲከፈቱና ግልጽ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል ናቸው፣

Federal Democratic Republic of Ethiopia .Ministry of Transport Authority No. 1

## 3. በሁሉም ማህበራት ፕሮግራም ወጥቶላቸው የማይሸፈኑ መስመሮችን በብቸኝነት ለመስጠት፣

እስካሁን ባለው አሰራር የአገር አቋራጭ ትራንስፖርት ማህበራት የጋራ ፕሮግራም በማውጣት በባለሥልጣኑ መ/ቤት እያፀደቀ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ማህበራት በጋራ የሚከፍቷቸውን አዳዲስ መስመሮች በባለቤትነት ይዞና ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማልማት እየተቻለና ተደራሽነትን በማስፋት አገልግሎቱን ማዳረስ ሲቻል ይህ ተፈፃሚ ባለመሆኑ ችግር መፈጠሩና ፕሮግራም ውስጥ ተካተው የማይሸፈኑ መስመሮችን በመለየት ሲሰሩ በሚፈልጉ ማህበራት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በብቸኝነት እንዲሰሩበት ማድረግ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ መሠረት የማይሸፈኑ መስመርችን በብቸኝነት ለመስጠት ከዚህ በታች ባሉት የአሰራር ቅደም ተከተል መፈፀም ይኖርበታል።

3.1 የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት ክትትል መናኸሪያ አስተዳደር ቡድን የማይሸፈኑ መስመሮችን በመለየት በመናኸሪያ አስተዳደር በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይለጥፋል እንዲሁም ለማህበራት በደብዳቤ ይገልፃል። ፕሮግራም ወጥቶላቸው ያልተሸፈኑ መስመሮች ትራንስፖርት ባለሥልጣን በማንኛውም ጊዜ በብቸኝነት የመስመር አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ ገብተው እንዲሸፈኑ ያደርጋል። ይህም ወር በገባ ከ21-25 ባሉት ቀናት ውስጥ ይከናወናል፣

3.2 የመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ/የአገር አቋራጭ መናኸሪያ/ የጨረታ ሣጥን ያዘጋጃል። የጨረታ ሣጥኑ ይዘት ሁለት ቁልፍ ያለው ሆኖ አንደኛው ቁልፍ በመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ እጅ እና ሁለተኛው ቁልፍ በማህበራት ተወካይ እጅ ይቀመጣል። የጨረታ ሣጥኑ ሲከፈትም ሆነ ሲታሸግ የማህበራት ስራ አስኪያጆች ወይም በማሕበሩ በስራ አመራር ቦርድ የፅሁፍ ውክልና ያለው ተወካይ እና በመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ በጋራ ይሆናል፣

3.3 ማህበራቱም በብቸኝነት መስራት የሚፈልጓቸውን መስመሮች ማስገቢያ ቀን ወር በገባ እስከ 5ተኛው ቀን ሆኖ ቅዳሜና እሁድንም ይጨምራል። በነዚህ ቀናት ውስጥ

በብቸኝነት ለመስራት የሚፈልጓቸውን መስመሮች በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፣

3.4 በአገር አቋራጭ መናኸሪያ አስተዳደር ቢሮ ውስጥ በስድስተኛው ቀን የማህበራት ስራ አስኪያጆች ወይም በማሕበሩ በስራ አመራር ቦርድ የፅሁፍ ውክልና ያለው ተወካይ በተገኙበት የጨረታ ሣጥን ይከፈታል። የጨረታ ሣጥኑን የመክፈቻ ጊዜ ከ4:00 እስከ 4:10 ባለው ጊዜ ውስጥ ሆኖ ሂደቱን በተገኙት አባላት ቃለጉባኤ በመያዝና በመፈራረም ተግባሩ ይከናወናል፣

3.5 የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት ክትትል መናኸሪያ የአስተዳደር ቡድንም የተሰጣቸውን ግብረ መልስ በማጠናከር የሁሉም ማህበራት ሥራ አስኪያጆች ወይም በማሕበሩ በስራ አመራር ቦርድ የፅሁፍ ውክልና ያለው ተወካይ በተገኙበት ከአንድ በላይ ማህበራት ምርጫቸው በሆነው መስመር ላይ በዕጣ እንዲለዩ ያደርጋል፣

3.6 ከአንድ በላይ ማህበራት በተመዘገቡበት መስመር የዕጣ አወጣጡ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ እንዲመዘገብ ይደረጋል። ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በቀዳሚነት ዕጣ የወጣለት ማህበር በገባው ውል መሰረት መስመሩን በብቸኝነት ይወሰዳል።

3.7 በመጀመሪያ የዕጣ አወጣጥ መሰረት ዕጣው የወጣለት ማህበር በብቸኝነት እንዲሸፍነው ለማድረግ መስመሩ ተነሺ በሆነበት መናኸሪያ የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት ክትትል መናኸሪያ አስተዳደር ቡድን ጋር የውል ስምምነት ይፈጸማል፣/የስምምነት ውሉ ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዞ ይቀመጣል፣

3.8 በብቸኝነት የሚሰጥ መስመር የውል ስምምነት በ3 ኮፒ ይዘጋጃል። አንደኛው በውል ሰጪ እጅ፣ 2ኛው በውል ተቀባይ እጅ 3ኛው ደግሞ በሕዝብ ትራ/አገ/ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት በሰነድነት ይቀመጣል፣

3.9 በብቸኝነት መስመሩን የወሰደው ማህበር በማንኛውም ዘዴ/ስልት/ማለትም በድጎማ፣ በማካካሻና ምድብተኛ ተሽከርካሪ ከሌለ ሌላ ምትክ ተሽከርካሪ በመመደብ መስመሩን የማሸፈን ግዴታ አለበት። በዙር መስመር ላይ የተመደቡ ተሽከርካሪዎችን በብቸኝነት መስመር ላይ መድቦ ማሰራት የተከለከለ ነው። የወሰደውን መስመር ከተዋዋለበት ጊዜ ጀምሮ በወሩ ውስጥ ለ20 ቀናት መስመሩን ማሸፈን አለበት። መስመሩን ማሸፈን ካልቻለ ውሉ ተቋርጦ መስመሩ በዕጣ 2ኛ ለወጣው ማህበር በውል እንዲሰጥ ይደረጋል።

3.10 በተራ ቁጥር 3.7 ሳይ የተጠቀሰው እንዳስ ሆኖ በብቾኝነት የወሰደውን መስመር መሸፈን ያልቻስ ማህበር በአገራዊው የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የዲሲፒሊን እርምጃ ይወሰድበታል::

3.11 በብቸኝነት መስመሩ ተሰጥቶት ባስመሥራቱ ውስ የተቋረጠበት ማህበር በመስመሩ ስመጠቀም ዳግም ጥያቄ ማቅረብ የሚችስው መስመሩ በጋራ ፕሮግራም ውስጥ ተካቶ በባስሥልጣኑ መ/ቤት ሲፀድቅ ብቻ ነው::

3.12 በብቾኝነት የተሰጡ መስመሮችን የትኬት አቆራረጥ በተመስከተ መስመሮቹ እንዲስማመዱና ውጤታማ እስከሚሆን ድረስ የትኬት አቆራረጥ ቦታው የት መሆን እንዳስበት የመናኸሪያው አስተዳደር መሪ ይወስናል::

3.13 ማህበራት በብቾኝነት መስመር ሳይ ስመስራት በህገደንባቸው መሠረት የዘመኑ የታደሰ የማህበር የምዝገባ ፈቃድ ማረጋገጫ ሲኖራቸው ብቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል::

## 4. <u>በትራንስፖርት ባለሥልጣንና በክልሎች እንዲሁም በማህበራት በጋራ ተጠንተው የሚከፈቱ መስመሮችን በተመለከተ፡-</u>

4.1 በትራንስፖርት ባስሥልጣን፣ በክልሎች፣ በሕዝብ ጥያቄ እና ማህበራት በጋራ ተጠንተው የሚከፍቷቸው መስመሮች በጋራ ፕሮግራም ውስጥ ገብተው እንዲሸፈኑ ይደረጋል::

4.2 በትራንስፖርት ባስሥልጣን/በክልሎች/ተጠንተው የሚከፈቱ መስመሮች እኩል ዕድል ማህበራት/ድርጅቶች እንዲያገኙ ይደረጋል:: ነገር ግን በነባር አገልግሎት እየሰጡ በሚገኙ የአገር አቋራጭ መደበኛ የሥምሪት መስመሮች ሳይ ተጽእኖ የማይፈጥር መሆኑ ይረጋገጣል::

4.3 በአዲስ በሚጠናው መስመርና በነባሩ መስመር መካከል ያስው ርቀት 50 ኪ.ሜትርና በሳይ የሆነ እንዲሁም አዲሱ መስመር ከተሠጠ በኋሳ ስንፅፅር እንዲያመች የሚጓጓዙ ተሳፋሪዎች ቁጥር መቀነስ አስመቀነሳቸው እና ነባር መስመሮች አፈፃፀማቸው ከ66.66% በታች መሆናቸውን በመናኸሪያው አስተዳደር ቡድን መሪ እየተረጋገጠ ሲቀርብ ብቻ ተግባራዊ ይደረጋል::

4.4 ማህበራት በጋራ ማጥናት የሚፈልጉትን መስመሮች መስመሩ በሚነሳበት መናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ በደብዳቤ ጥያቂያቸውን ማቅረብ አስባቸው::

4.5 ማህበራት በጋራ ማጥናት የሚፈልጉትን መስመሮች ላይ መስመሩ በሚነሳበት መናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ መፈቀድ አስመፈቀዱን በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል::

4.6 እንዲያጠኑ ፈቃድ ካገኙ በኋላ ማህበራት በጋራ በመሆን በአንድ ወር ውስጥ አጥንተው መስመሩ ተነሺ በሆነበት መናኸሪያ ለመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

4.7 በማህበራት በጋራ ተጠንተው የሚከፈቱ መስመሮች በቅድሚያ በመደበኛ ፕሮግራም ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል:: በፕሮግራም ተካተው የማይሸፈኑ መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ አፈፃፀሙ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጾች ስር በተቀመጠው አግባብ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

# 5. በማህበር በግል ተጥንተው ስለሚከፈቱ የብቸኝነት መስመሮች

5.1 አንድ ማህበር በብቸኝነት በአንድ ጊዜ ከሦስት መስመር በላይ ለማጥናት ጥያቄ ማቅረብ አይችልም:: ሆኖም ሌሎች ማህበራት የተጠየቁትን መስመሮች ለማጥናት ፍላጎት ከሌላቸው ቁጥሩ አይገደብም::

5.2 አንድ ማህበር ለብቻው አጥንቶ ሊከፍት የፈለገውን መስመር በብቸኝነት ለመስራት እንዲችል እንዲፈቀድለት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራ/ስምሪት ክትትልና የመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ /በአገር አቋራጭ መናኸሪያ/ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለበት:: በጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገቢያ ጊዜ ወር በገባ ከ21 እስከ 25 ባሉ ጊዜያት ውስጥ ብቻ ይሆናል::

5.3 በአገር አቋራጭ መናኸሪያ አስተዳደር ቢሮ ውስጥ በ26/በሃያ ስድስተኛ/ ቀን የማህበራት ስራ አስኪያጆች ወይም በማሕበሩ በስራ አመራር ቦርድ የፅሁፍ ውክልና ያለው ተወካይ በተገኙበት ሣጥኑ ይከፈታል::

5.4 አንድን መስመር ለማጥናት ሁለት እና ከዛ በላይ ማህበራት/ድርጅቶች ካቀረቡ እና በጋራ ለማጥናት ስምምነት ካልተደረሰ በዕጣ እንዲለዩ ይደረጋል::

5.5 ማሕበሩ በግል ያጠናቸውን መስመሮች ለትራንስፖርት ባለስልጣን የማቅረቢያ ጊዜ በአመት 2/ሁለት/ጊዜ ብቻ ይሆናል ::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

5.6 አዲስ የሚከፈቱ መስመሮች በነባር በፕሮግራም ተካተው ያሉ የአገር አቋራጭ መደበኛ መስመሮች ላይ ተፅዕና የማይፈጥሩ መሆናቸውን ነባር መስመሮች አፈፃፀም ከ66.66% በታች መሆናቸው ሲረጋገጥ፣ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመስክ ምልከታ በማድረግ ሲረጋገጥ ስጠያቂው አካል እንዲያጠና ማመልከቻ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ፈቃድ ይሰጣል፣

5.7 በአዲስ በሚጠናው መስመርና በነባሩ መስመር መካከል ያለው ርቀት 50 ኪ.ሜትርና በላይ የሆነ እንዲሁም አዲሱ መስመር ከተሠጠ በኋላ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ለንፅፅር እንዲያመች የሚጓጓዙ ተሳፋሪዎች ቁጥር መቀነስ አለመቀነሳቸው እና ነባር መስመሮች አፈፃፀማቸው ከ66.66% በታች መሆናቸውን በመናኸሪያው አስተዳደር ቡድን መሪ ተረጋግጦ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ሲቀርብና ሲረጋገጥ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

5.8 መስመሩን እንዲያጠና የተፈቀደለት ማህበር የፈቃድ ደብዳቤ ከደረሰበው ቀን ጀምሮ በተቀመጠው የማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ አጥንቶ መስመሩ ለሚነሳበት መናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ ማቅረብ አለበት፡፡

5.9 ማህበሩ እንዲያጠና የተሰጠውን መስመር በተቀመጠው የማቅረቢያ ጊዜ ማቅረብ ያልቻለ ከሆነ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡ ሌላ ማህበር በመስመሩ ላይ ጥያቄ ካቀረበ በብቸኝነት በሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

5.10 ጥናቱን ያጠናው እና የቅድሚያ መብት ያገኘው ማህበር ውል ይዋዋላል፣ ውሉ በብቸኝነት የአሰራር ስርዓት አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.7 መሠረት ይሆናል፡፡

5.11 በብቸኝነት መስመር ላይ ለመስራት ፈቃድ ያገኘ ማህበር በነባሩ መስመር ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ /አለመፈጠሩን/ ለማረጋገጥ ጊዜያዊ ፈቃድ ለሁለት ወር ትራንስፖርት ባለሥልጣን ይሰጠዋል፡፡ በሁለት ወር ውስጥ የተከፈተው የብቸኝነት መስመር በነባሩ መስመር ላይ ምንም ተፅዕኖ የማይፈጥር መሆኑ በመረጃ ሲረጋገጥ የውል ስምምነት እንዲፈፅም ይደረጋል፡፡

5.12 በብቸኝነት የተሠጡ መስመሮች አገራዊ የአፈፃፀም መመሪያ ሳይከተል ማለትም 50%ተሳፋሪ አልተገኘም ሳይባል የተገኘውን ተሳፋሪ በመያዝ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡ መስመሩን ማሸፈን ካልቻለ ውሉ ተቋርጦ መስመሩ ወደ መደበኛ ፕሮግራም በማካተት አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በውሉ መሠረት ያልፈጸመ ማህበር ከላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3.10 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5.13 አንድ ማህበር መስመሩን በብቸኝነት ወስዶ ማሽፈን ባለመቻሉ መስመሩ ከተወሰደ በኋላ በመስመሩ የመጠቀም መብት የለውም፡፡ ሆኖም ግን መስመሩ በጋራ ፕሮግራም ውስጥ ሲገባ የመጠቀም መብት ይኖረዋል፣

5.14 አንድ ማህበር አጥንቶ መስመሩን ከወሰደ በኋላ በውሉ መሠረት መፈፀምካልቻለ የመስመር አሠጣጡ የደረጃ 1፣ 2ና 3 ማህበራት በብቸኝነት በሚሰጥ የአሰራር ስርዓት መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ አፈፃፀሙ በብቸኝነት አሰራር ስርዓት በአንቀጽ 3 ስር ባሉ ንዑስ አንቀፆች ከ3.1፣ 3.2፣ 3.3፣ 3.4 እና 3.6 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 6. የብቸኝነት መስመሮችን በጋራ ስለመስራት

የብቸኝነት መስመሮችን በጋራ ስመስራት አስፈላጊነት ማህበራት አቅማቸውን አጠናክረው በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የጋራ ተጠቃሚነት በማገልበት የትራንስፖርት ተደራሽነትን በማረጋገጥ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

አንድ ማኅበር በብቸኝነት ለመሥራት የወሰደውን መስመር ከሌላ ማህበር በጋራ መሥራት የሚችለው፡-

6.1 የብቸኝነት መስመሮች የጋራ ስምምነት ተግባራዊ የሚሆነው በተመሳሳይ ደረጃ በሚገኙ ተሽከርካሪዎች ነው፡፡

6.2 የወሰደውን ወይም ያጠናውን መስመር ከትራንስፖርት ባለሥልጣን ጋር ውስታ ወስዶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 20 ቀናት ወይም 66.66% መሸፈኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

6.3 ሁለት ወይም ሦስት ማህበራት በጋራ ስምምነት የብቸኝነት መስመሮች ላይ መስራት ይችላሉ፣ በጋራ ስምምነት መሠረት እኩል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.4 ማህበራት በጋራ ስምምነት የብቸኝነት መስመሮችን መስራት የሚችሉት በትራንስፖርት ባለሥልጣን ሲፀድቅ እና ማረጋገጫ ሲሰጥ ብቻ ይሆናል፣

6.5 ማህበራት የጋራ ስምምነታቸውን የመስመር ስም እና ብዛት በፅሁፍ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

6.6 በጋራ ስምምነት የሚሠሩ የብቸኝነት መስመሮች ብዛት ከሁለት ወይም ከሦስት መብለጥ የለባቸውም፣

6.7 በጋራ ስምምነቱ መሠረት በመስመሩ የጋራ ስምምነት ያደረጉ ማህበራት እኩል ተጠያቂነት አለባቸው፣

6.8 በብቸኝነት በጋራ ስምምነት የተሰጡ መስመሮች ውስን ለማቋረጥ የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል፡፡

6.9 ቀድሞ የጋራ ስምምነት የተደረሰበት ለሌላ ማህበር የብቸኝነት መስመር የጋራ ስምምነት ሆኖ አያገለግልም፣

6.10 የጋራ ስምምነቱ የሚታደሰው በማህበራት የጋራ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በብቸኝነት መስመሩ የቀይታ ጊዜ የተገደበ ይሆናል፣

6.11 የጋራ ስምምነቱ አዲስ የሚከፈቱ ወይም አገልግሎት እየሠጡ ያሉ የብቸኝነት መስመሮችን ሲያካትት ይችላል፣

## 7. የብቸኝነት መስመር የቆይታ ጊዜ

7.1 በብቸኝነት መስመሩን ወስዶ በብቸኝነት አሠራር ሥርዓቱ መሥፈርት መሠረት አገልግሎት መስጠት የቻለ ማኅበር ውሉ በየዓመቱ ይታደሳል፡፡

7.2 በብቸኝነት የአሠራር ሥርዓት መሥፈርት መሠረት አገልግሎት መስጠት የቻለ ማኅበር 3/ሶስት/ ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ይኖረዋል፡፡ መስመሩን ለማልማት ብዙ ጊዜ የወሰደ፣ ብዙ ወጪ ያወጣ ከሆነና ይህም ማህበሩ ለአባል ተሽከርካሪ ድጎማ ያደረገበት የክፍያ ደረሰኝ ሲያቀርብ፣ ባለንብረቱ መስመሩን ለመሸፈን የወሰደበት ጊዜ የስምሪት ፕሮግራም ሲረጋገጥ፣ ለጥገና ያወጣው ወጪ ከህጋዊ ጋራዥ ህጋዊ ማስረጃ ሲያቀርብ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ለመሸፈን ብዙ ጊዜ የወሰደበት ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ ሲቀርብ እና አፈፃፀሙ ሳይቆራረጥ 66.66% በላይ ከሆነ በመረጃ የተደገፈና የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ሲያረጋግጥ መስመሩ በድጋሚ ለስድስት ወር ይታደስለታል፡፡

7.3 3/ሶስት/ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ መስመሩ ወደ ጋራ ኘሮግራም እንዲገባ ይደረገል፡፡

7.4 በመደበኛ መስመር ተካቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሸፈን ካልቻለ በአዲስ መልክ የቀድሞ ማኅበሩ ፍላጎት ካለው ውሉን ማደስ ይችላል፡፡ ሆኖም የቀድሞ ማህበር ውሉን ለማደስ ፍላጎት ከሌለው ለሌሎች ማህበራት በብቸኝነት የአሰራር ስርዓት መሠረት ለውድድር ይቀርባል፡፡



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

## 8. የብቸኝነት መስመር በጨረታ/ውድድር ለመስጠት፣ ለማጥናት እና ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል የማስተናገጃ ጊዜ

8.1. በሁሉም ማህበራት ፕሮግራም ወጥቶላቸው የማይሸፈኑ መስመሮችን በብቸኝነት እንዲሰሩ በማስታወቂያና ለማህበራት በደብዳቤ የማሳወቂያ ጊዜ ወር በገባ ከ21 እስከ 25 ባሉት ጊዜያት ውስጥ ይሆናል፡፡

8.2. ማህበራት በደብዳቤና በማስታወቂያ በተገለፀላቸው መሠረት በብቸኝነት ለመስራት የማወዳደሪያ ጊዜ ወር በገባ በ26ኛው ቀን ይሆናል፡፡

8.3. ማህበራት በግል ያጠኗቸው የብቸኝነት መስመሮች የማቅረቢያ ጊዜ የመጀመሪያው ከሰኔ 25 እስከ ሐምሌ 24 እና የሁለተኛው ከጥር 25 እስከ የካቲት 24 ባሉት ጊዜያቶች ብቻ ይሆናል፡፡

8.4. ማህበራት በግል አጥንተው የሚከፍቷቸው የብቸኝነት መስመሮች ሥራ የሚጀምሩበት ጊዜ በአመት ሁለት ጊዜ ይሆናል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ እና የሁለተኛው ከመጋቢት 1 ቀን ጀምሮ ባሉት ጊዜያቶች ብቻ ይሆናል፡፡

## 9. የአሰራር ስርዓቱ ተግባራዊነት

ይህ የተሻሻለው የአሰራር ስርዓት ቀድመው በተሰጡት የብቸኝነት መስመሮች ላይ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

## 10. የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን

ይህን የአሰራር ስርዓት ለማሻሻልም ሆነ ለመሻር ሥልጣን ያለው የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡

## 11. ይህ የአሰራር ስርዓት የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የአሰራረ ስርዓት ከፀደቀበት ከሚያዝያ ወር/2008 ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም

የትራንስፖርት ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

# የትራንስፖርት ባለሥልጣንና ማህበራት መካከል በብቸኝነት የሚሰጡ መስመሮች ውል

## ክፍል አንድ

### 1. *አጭር ርዕስ*

ይህ ውል “በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግልት ሽፋን ያላገኙ መስመሮችን በብቸኝነት በመስጠት መስመሮቹ እንዲሰሙና ተደራሽነት እንዲሰፋ በማድረግ የአገልግሎት ፈላጊውን ሕብረተሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ የተደረገ ውል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::”

### 2. *ተዋዋይ ወገኖች*

በአንድ ወገን ተዋዋይ የትራንስፖርት ባለሥልጣን አድራሻ አዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ቂርቆስ ወረዳ 7 ስልክ ቁጥር 0115510244 ፖ.ሣ.ቁ. 2504 “ውል ሰጪ” እየተባለ በሚጠራውና በሌላ ወገን ውል ተቀባይ እየተባለ በሚጠራው ______________ የሕዝብ ማመላለሻ የግል ባለንብረቶች ማህበር አድራሻ ______ ወረዳ __________ ስልክ ቁጥር እየተባለ በሚጠራው መካከል የተደረገ የውል ስምምነት ነው::

### 3. *የውሉ ዓላማ*

1. በአገር አቋራጭ ትራንስፖርት አገልግልት በመርሐ ግብር ውስጥ ገብተው የማይሸፈኑ መስመሮችን በመለየት በብቸኝነት እንዲሰራባቸው በማድረግ አገልገሎቱ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው::

2. በማህበራት መካከል ጤናማ ውድድር ተፈጥሮ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግና ተጨማሪ መስመሮች በብቸኝነት እንዲከፈቱ ማስቻል ነው::

# ክፍል ሁለት

## የውል ሰጪ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

4. ውል ሰጪ የሚከተሉት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ይኖሩታል

1. የወጣው የአሰራር ስርዓት በተደረሰበት የውል ስምምነት መሰረት መፈጸሙንና መተግበሩን ይከታተሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል።
2. በአፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይስያል፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል ውሳኔም ይሰጣል፣
3. በውሉ መሰረት መስመሩን በብቸኝነት የወሰደው ማህበር በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት መሸፈን ካልቻለ የሕዝብ ትራንስፖርት ስ/ክ/የመናኸሪያ አስተዳደር ቡድኖች በአገራዊ የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የድስፒሲን ርምጃ ይወስዱበታል፣
4. በብቸኝነት የተሰጡ መስመሮች ላይ ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር የአሰራር ስርዓት ያወጣል፣ የአገልግሎት መቆራረጥ እንዳይኖር ይደግፋል፣ ያበረታታል፣
5. በብቸኝነት የሚሰጡ መስመሮች ግልፅና ፍታዊ በሆነ መንገድ መስጠታቸውን ያረጋግጣል፣
6. በብቸኝነት የተሰጡ መስመሮች በወጣው የአሰራር ስርዓት መሰረት ያስመተገበራቸው ሲረጋገጥ ውሉን የመሰረዝ፣

5. የውል ተቀባይ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች

- ውል ተቀባይ የሚከተሉት ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣
  - በውሉ የወሰደውን መስመር በየጊዜው እየተከታተለ ባለው የአሰራር ስርዓት መሰረት ተሽከርካሪዎችን የመመደብ፣
  - ለሚጓጓዘው መንገደኛ አስፈላጊውን ክብካቤ ማድረግና የተሟላ አገልግሎት ማግኘቱን የማረጋገጥ፣
  - በሕግ የተቀመጠውን የትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ ብቻ ማስከፈል፣
  - በብቸኝነት የወሰደውን መስመር አስመልክቶ ትክክለኛውን ሪፖርት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የማቅረብ፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

- ማህበሩ በየጊዜው የሚመድባቸው ተሽከርካሪዎችን የደህንነት ሁኔታ የማረጋገጥና በመኪናው ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች አስፈላጊውን ሰነድ አሟልተው መገኘታቸውን የማረጋገጥ፣
- ተሽከርካሪው በተሰጠው ስምሪት አግባብ ከመነሻ-መድረሻ አገልግሎት መሰጠቱን የማረጋገጥ፣
- ሌሎች ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚሰጡ የአሰራር መመሪያዎች ተቀብሎ በሥራ ላይ የማዋል፣

# ክፍል ሦስት

## 3. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 3.1 የውል መታደስ

ውል ተቀባይ በብቸኝነት የወሰደውን መስመር በአሰራር ስርዓቱ መሰረት አሟልቶ አገልግሎት መስጠቱ ሲረጋገጥ ውሉ በየዓመቱ ይታደስለታል፣

### 3.2 ውሉ በሕግ ፊት ስላለው ተቀባይነት

ይህ ውል በሕግ ፊት የፀና ይሆናል

### 3.3 የውሉ መፈረም

ይህ ውል የሚፈርሰው ማህበሩ በብቸኝነት የወሰደውን መስመር እንደ አሰራር ስርዓትና እንዲውሉ መፈጸም ሳይችል ሲቀር በሚሰጠው የቅድሚያ የአንድ ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ውሉ ሲፈርስ ይችላል፣

### 3.4 የውሉ መፈራረም

ይህ ውል በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ተፈርሞበትና ክብ ማህተም ተደርጎበት በሁለቱም እጅ እንዲቀመጥ ይደረጋል፣

### 3.5 ውሉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ውል በብቸኝነት የሚሰጡ መስመሮችን አስመልክቶ በተዘጋጀው የአሰራር ስርዓት መሰረት እስከተከናወነ ድረስ ለሦስት ዓመት የፀና ይሆናል::

***ውል ሰጪ***

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ቀን ____________________

***ውል ተቀባይ***

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ቀን ____________________